
# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-30/2017 የነበረው
# የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈው የኖቨምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሓያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ አመዝኖ የቆየ ሲሆን፤ በተጨማሪም በመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ከተጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በቦታ ሥርጭትም ሆነ በመጠን የተስፋፋ ዝናብ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ምሥራቅና በምዕራብ ኢትዮጵያ ላይ የተመዘገበ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎችም ላይ ከባድ ዝናብ ተስተውሏል፡፡ ለመጥቀስም ያህል በምዕራብ አባያ 106.0፣ በሞያሌ 69.7፣ በቦሬ 39.4፣ በአዴት 43.2፣ በአቦቦ 39.5፣ በሀገረማርያም 63.6፣ እና በዶሎመና 47.3 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ በመጀመሪያው አስር ቀናት ከነበረው የደመና ሽፋንና ዝናብ ጋር ተያይዞ እምብዛም ያልተጠናከረ ቢሆንም፤ በሁለተኛውና በሶስተኛው አሥር ቀናት ግን ከደመና ሽፋን መቀነሰ ጋር ተያይዞ የማለዳውና የሌሊቱ ቅዝቃዜ ተጠናክሮ የቀጠለ በመሆኑ በአብዛኛው የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። በወሩ ውስጥ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ2 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በደብረ ብርሃን -1.6፣ 0.2 እና 1.4፣ በመሀል ሜዳ -1.2፣ በሀሮማያ 0.0 እና 1.6፣ በወገል ጤና 0.5፣ በአምባ ማርያም 1.0፣ በአርሲ ሮቤ 1.0 ፣ በባቲ 1.6፣ በአዲግራት 2.0፣ በደብረዝት 2.0፣ አዲስ አበባ ቦሌ ኢንጂነሪነግ 2.0፣ በቡኢ 2.0፣ መመዝገቡን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡


ባለፈው ወር የዘነበው ዝናብ ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-158 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከትግራይ የመካከለኛው፣ የምስራቀና የደቡብ ትግራይ፤ ከአማራ የባህርዳር፣ አዊ ዞን፣ ምዕራብ ጎጃምና የደቡብ ወሎ ኪስ ቦታ ዞኖች፤ ቤንሻጉል-ጉሙዝ ፤ጋምቤላ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ከኦሮሚያ ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጅማ፣ አርሲና ባሌ እንዲሁም የሊበን ዞኖችና አብዛኛው ሶማሌ ከ5-17 ቀናት ያህል ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ቦታዎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 6 እና 7) ።

ባለፈው ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር የመካከለኛው ትግራይ፤ ከኦሮሚያ ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ አርሲና ባሌ እንዲሁም አብዛኛው የሊበን ዞኖች፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ፣ የሲዳማና ጌዶ እንዲሁም የደራሼ፣ የኮንሶና የቡርጂ ዞኖች፤ ጋምቤላ፣ ከሶማሌ ክልል የደገሀቡር ፣ የቆራሂ፣ የጎዴ፣ የአፍዴርና የሊበን ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው። የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ የአየር ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል (ካርታ 8) ።


ካርታ6   ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ7 ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ8   ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-30/2017 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው የኖቨምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በአብዛኛው የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝናባቸው የቆየ ነበር፡፡ ይህም በመሆኑ የክረምት ተጠቃሚ የነበሩት የሀገሪቱ ክፍሎች አሁን በደረቅ የአየር ሁኔታ ላይ ያሉ ስለሆኑና በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑ ሥፍራዎች ላይ ደግሞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እየጨመረ በመምጣቱ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች አሉታዊ ጎን ሊያሳድር ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በወሩ ውስጥ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ በመኖሩ ምክንያት የተገኘው እርጥበት ዘግይተዉ ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የተገኘው እርጥበት በአካባቢው በዝናብ መቆራረጥ ምክንያት ተገልብጦ በድጋሚ ለተዘሩ ሰብሎች አዎንታዊ ጎን ነበረው። በአንጻሩ ደግሞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ የተገኘዉ እርጥበት በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ እንደነበረው እሙን ነው (ካርታ 9)።


ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2017 የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-30/2017 የነበረው የአየር ጠባይ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባለፈው የኖቬምበር ወር የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በጥቂት የደቡብ ምዕራብና የደቡብ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል$ በዚህ መሰረት ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች ጥቂት የመካከለኛው ስምጥሸለቆ እንዲሁም የላይኛውና የታችኛው ገናሌዳዋ ተዋሳኝ ቦታዎች ሲሆኑ፤ መጠነኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ደግሞ አብዛኛው ገናሌዳዋ፣ የላይኛው ባሮአኮቦ፣ የአባይ ደቡባዊው ክፍል፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆና የታችኛው ኦሞጊቤ ተፋሰሶች ናቸው$ በተጨማሪም በከፊል ደረቅ ሁኔታ የነበራቸው የዋቢሸበሌ ምዕራባዊው አጋማሽ ኪስ ቦታዎች፣ ጥቂት የላይኛው ስምጥሸለቆና ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛው አባይ ደቡባዊው ክፍል እና የገናሌዳዋ ተፋሰሶች ናቸው$ የተቀሩት አብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል (ካርታ 10)$

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2017 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## ከዲሴምበር 1-31/2017 የሚኖረው

## የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በዲሴምር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ከመዘውተሩ በላይ በአንዳንድ ደጋማ ሥፍራዎች ላይም የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ የሚያይልበትና አልፎ አልፎ ደግሞ የቅዝቃዜ መጠኑ ከዜሮ ዲግሪ ሴልስየስ በታች የሚወርድበት አጋጣሚ አለ፡፡

በሚቀጥለው ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ  እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞም በተለይም በደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚጠናከር ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ሌላ በጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ ክፍሎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራል፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-31/2017 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የዲሴምበር ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት አከባቢዎች የመኸር ሰብሎች የእድገት ጊዜያቸውን ጨርሰው ለመሰብሰብ የሚደረሱበት ወር ነው፡፡ በሚቀጥለው የዲሴምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚጠናከር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይም ውርጭ ሊከሰት እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ:: ይህም ደረቅ ሁኔታ የእድገት ጊዜያቸውን ለጨረሱና ተጨማሪ የውሃ አቅረቦት ለማይፍልጉ ሰብሎች እንዲሁም የእድገት ጊዜያቸውን ጨርሰው ለመሰብሰብ ዝግጁ የሆኑ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ፤ አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸዉ አካል የደረሱ ሰብሎችን መሰብሰብ ይኖርባቸዋል:: በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይ ሊከሰት የሚችለው ውርጭ ዘግይተው ለተዘሩትና ፍሬ ማፈራት ደረጃን ያላለፉት ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በተዳከመ ሁኔታ ቢሆንም በደቡብ ኦሮሚያ የኢትዮያ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩትና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱት የመኸር ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዲሁም ለአርብቶ

አደሩና ለከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢዎች የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሟላትና ለእፅዋት ልምላሜ መሻሻል ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሰምበር 1-31/2017 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የዲሰምበር ወር በአብዛኛው የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ነፋሻማና ፀሃያማ ሁኔታ የሚዘወተርበት ወር ነው። ይህንን ተከትሎ በተለይም በላይኛው የተፋሰስ ክፍል የገፀምድርና የከርሰምድር ውሃ መገኘት እየቀነሰ የሚሄድበት ሁኔታ ይስተዋላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚቀጥለው ወር የበጋው የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረውና ደረቅ ሁኔታ እንደሚያመዝን ይጠበቃል፡ በሌላ በኩል በጥቂት የላይኛው ባሮአኮቦና የመካከለኛው ኦሞጊቤ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል:: በተቀሩት ተፋሰሶች ላይ የበጋዉ የአየር ጠባይ ለከርሰ ምድርና ለገጸምድር የውሃ ክምችት መቀነስ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር ውሃን አግባብ ባለው ሁኔታ መጠቀም ተገቢ ነው።